# ኢየሱስን መከተል

**ለእያንዳንዱ ታሪክ መሪው የሚከተሉትን ሀሳቦች ያዘጋጃል፡-**

1. የባለፈውን ሳምንት ታሪክ ክለሳ
2. አንድን ታሪክ በአውድ (context) ለማስቀመጥ የሚረዳውን መግቢያ
3. የቃል ጥናት ክፍሎችን ይመርጣል፡፡
4. ተጨማሪ የመወያያ ጥያቄዎችን

አራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች

1. ከዚህ ታሪክ ስለ ኢየሱስ ወይም ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ?
2. በታሪኩ ውስጥ ከተገለጹ ሰዎች ተነስተን ስለ ሰው ምን እንማራለን?
3. ኢየሱስ ዛሬ ምን እያስተማረህ ነው?
4. ኢየሱስ በዚህ ታሪክ እንዳደረገ እንዴት ሰዎችን ደቀመዝር ማድረግ እንችላለን?

## ታሪኮች፡-

1. ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ መሰከረ- ዮሐ፡1፡19-37
2. ኢየሱስን ማግኘት- ዮሐ፡1፡37-51
3. የደቀመዝሙርነት ጥሪ- ሉቃ፡5፡1-11
4. ኢየሱስ ርኩስ መንፈሱን አስወጣው- ማር፡1፡21-39
5. ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን መረጠ- ሉቃ፡6፡12-23
6. የተራራው ስብከት (ክፍል፡1)- ሉቃ፡6፡27-36
7. የተራራው ስብከት (ክፍል፡2)- ሉቃ፡6፡37-49
8. ዘሪ ሊዘራ ወጣ- ማቴ፡12፡46-13፡23
9. ኢየሱስ ይፈውሳል- ማር፡5፡1-20
10. ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ላካቸው - ማቴ፡9፡35-10፡17
11. ኢየሱስ 5000 ሺህ ሕዝብ መገበ - ማቴ፡14፡13-23
12. ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ- (ክፍል፡1) ዮሐ፡6፡22-46
13. ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ (ክፍል፡2) - ዮሐ፡6፡48-69
14. የጴጥሮስ ንስሐ - ማቴ፡16፡13-27
15. የኢየሱስ በሐዋሪያት ፊት መለወጥ - ማቴ፡17፡1-13
16. ለወንድምህ ይቅርታ ማድረግ - ማቴ፡18፡15-35
17. ኢየሱስን መከተል የሚያስከፍለው ዋጋ - ሉቃ፡9፡57-10፡1
18. የጌታ ፀሎት - ሉቃ፡11፡1-13
19. ደቀመዝሙር መሆን የሚያስከፍለው ዋጋ - ሉቃ፡14፡25-35
20. የበግና የድሪም ምሳሌ - ሉቃ፡15፡1-10
21. የጠፋው ልጅ - ሉቃ፡15፡11-32
22. የአልዓዛር ከሞት መነሣት - ዮሐ፡11፡1-49
23. ሌሎችን ማገልገል - ማር፡10፡31-45
24. ኢየሱስ በድል ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ - ሉቃ፡19፡28-48
25. ኢየሱስ የደቀመዛሙርትን እግር አጠበ - ዮሐ፡13፡1-26
26. ኢየሱስ ወደ አብ የሚያደርስ መንገድ ነው - ዮሐ፡14፡1-18

27.ኢየሱስ እውነተኛ የወይን ግንድ ነው - ዮሐ፡15፡1-17
28.ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ፀለየ - ማር፡14፡32-42
29.የጴጥሮስ ክህደት - ሉቃ፡22፡54-62
30.የኢየሱስ ስቅለት - ማር፡15፡24-39
31.ኢየሱስ ሕያው ሆነ - ሉቃ፡24፡1-49
32.ኢየሱስ ለጴጥሮስ ትዕዛዝ ሰጠው - ዮሐ፡1-23
33. የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ - ሐዋ፡1፡1-10
34.የበዓለ ሃምሳው ቀን (ጴንጠ ቆስጤ) - ሐዋ፡2፡1-16
35.ጴጥሮስ - ሐዋ፡3፡1-21
36.የዲያቆናት (አገልጋዮች) መሾም - ሐዋ፡6፡1-8
37.ስደት - ሐዋ፡7፡54-8፡4
38.ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ደቀመዝሙር አደረገው - ሐዋ፡16፡1-5፣ 2ጢሞ፡2፡1-5

**<u>የቃል ጥናት ክፍሎች</u>**

1. ዮሐ፡1፡29
2. ማቴ፡4፡19
3. ዮሐ፡11፡25-26
4. ማር፡10፡43-45
5. ማቴ፡9፡37-38
6. ዮሐ፡6፡67-69
7. ማቴ፡16፡24-25
8. ሉቃ፡14፡26-27
9. ሉቃ፡19፡41-42
10. ዮሐ፡14፡15-17
11. 2ጢሞ፡2፡1-2

## <u>ትምህርት - 1</u>

**<u>ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ መሰከረ</u>**

**<u>መግቢያውን አንብብ</u>**፡- እነዚህ ተከታታይ ታሪኮች ደቀመዛሙርት ኢየሱስን ያገኙበት፣እርሱን የተከተሉበት፣እርሱን ያወቁበትና በእርሱ ማደግ የጀመሩበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ እነዚህ ታሪኮች በቅደም ተከተላቸው መሠረት ከአራቱ ወንጌላት የተወሰዱ ናቸው፡፡
ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ደቀመዛሙርት እንደ እርሱ እንዲሆኑና በዓለም ላይ የእርሱ ሠራተኞች እንዲሆኑ ወሰዳቸው፡፡ አንተም እንደ እነርሱ ምላሽ ከሰጠህ እንደ ኢየሱስ ደቀመዛሙርት ትሆናለህ ማለት ነው፡፡

የዚህ ሳምንት ታሪክ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ይናገራል፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ በምድረ በዳ ይሰብክ ነበር፡፡ ልብሱ የቅመል ቆዳ ሲሆን አንበጣን ይመገብ ነበር፡፡ ብዙ ሕዝብ እርሱን

ሊሰማ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ መጣ። ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡ ዮሐንስ ነገራቸው። ሕዝቡ ንስሐ ገብተው በዮሐንስ እጅ ተጠመቁ። አንድ ቀን ኢየሱስ ወደ እርሱ መጥቶ ተጠመቀ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፦

ታሪኩን ተናገር፦ ዮሐ፡1፡19-37
ማን? ምን? መቼ? የት? እንዴት? ለምን? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።
ታሪኩን አንብብ።
በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፦ በታሪኩ ውስጥ ችግር ያለው ሰው አለ? ለችግሩ መፍተሔ እንዴት ያገኛሉ? ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለ መሆኑ ምን ማረጋገጫ አለህ?

## ትምህርት- 2

### ኢየሱስን ማግኘት

**መግቢያ**፦ ኢየሱስ የዓለምን ሐጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ (ልጅ) እንደሆነ ዮሐንስ ይመሰክራል። ደቀመዛሙርት ለኢየሱስ የሰጡትን ምላሽ ዛሬ እንማራለን። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንሚከተለው ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር፦ ዮሐ፡1፡37-51
ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ።
በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፦ ስለ ደቀመዝሙርነት ከመጥምቁ ዮሐንስ ሕይወት ምን እንማራለን? ኢየሱስን ከአንተ ጋር እንዲከተል የምትጋብዘው ሰው ማነው?

## ትምህርት-3

### የደቀመዝሙርነት ጥሪ

**መግቢያ**፦ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ ተመለሰ። ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራትን ሲያደርግና ሲያስተምር የኢየሱስን ማንነት እያወቁ ሄዱ። ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ወደምትገኘው ቅፍርናሆም ሄደ። ከዚህ ቀጥሎ የሆነው ከዚህ በታች ቀርቧል፦ ሉቃ፡5፡1-11
ታሪኩን ተናገር። የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ የመወያያ ጥያቄዎች፦ በዚህ ታሪክ የተለወጠው ማነው? ለለውጡ መንስኤ የሆነው ነገር ምንድነው? የኢየሱስ ደቀመዝሙር ማለት ምን ማለት እንደሆነው ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?

## ትምህርት-4

**ኢየሱስ ርኩስ መንፈሱን አስወጣው፡ ማር፡1፡21-39**

**መግቢያ**፦ ኢየሱስ በአሣ ላይ ያደረገውን ተአምር የባለፈው ሳምንት ታሪክ ያሳያል፡፡ ደቀመዛሙርቱ በዚህ እጅግ ተገርመው የበለጠውን ሊከተሉት ወሰኑ፡፡ ቀጥሎ የሆነውን ነገር ስትሰማ ለኢየሱስ የምትሰጠውን ምላሽና ስለ ስልጣኑ አስብ፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል ቀጥሎ ቀርቧል፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፦ በኢየሱስ ስልጣንና በፈውሱ ላይ ምን ምላሽ አለህ? ኢየሱስ በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደ አርአያ ያስቀመጣቸው ሁለት የአምልኮ ልምዶች ምንድናቸው? ኢየሱስ በማለዳው የጥሞና ጊዜ ያየው መገለጥ ምንድነው? ቁ.38-39

## ትምህርት-5

**ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሐዋሪያት መረጠ፦ ሉቃ፡6፡12-23**

**መግቢያ**፦ ሕዝቡ ኢየሱስን መከተል ጀመሩ፡፡ ሕዝቡ ከእርሱ ጋር ሲጓዙ ኢየሱስ ሕብረትን ፈጠረ፡፡ በኋላም ለእርሱ ሐዋሪያት ሊሆኑ በሚችሉ ጥቂት ሰዎች ላይ የበለጠውን ትኩረት አደረገ፡፡ ኢየሱስ ይህንን አስፈላጊ ውሳኔ እንዴት እንዳ ወሰነ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፦ ኢየሱስ ሌሊቱን በሙሉ የፀለየው ለምንድነው? ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን የመረጠበት ዓላማ ምንድው? (ማር፡3፡14) የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እንዴት ተባረኩ?

## ትምህርት- 6

**የተራራው ስብከት፡ ሉቃ፡6፡27-36**

**መግቢያ**፦ ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን እንደመረጠ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ማስተማር ጀመረ፡፡ በማቴዎስ ወንጌል ላይ ማቴዎስ የኢየሱስን ትምህርት የተራራው ስብከት ይለዋል፡፡ የኢየሱስ ትምህርት ደቀመዛሙርትንና የሰሙትን ሰዎች በጣም ገረማቸው፡፡ ዛሬም በእኛ ጊዜ ይህንን በእግዚአብሔር መንግሥት መኖር የሚለውን ትምህርት ለማመን እንቸገራለን፡፡ የተራራው ስብከት መጀመሪያው ክፍል ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ኢየሱስ የሚያስተምረውን ነገር እንዴት ማድረግ እንችላለን? ከኢየሱስ ትምህርት የተነሣ በዚህ ሳምንት ምን ታደርጋለህ? በክፉ ሰው ወይም በክፉ ነገር ላይ ያለህ ምላሽ ምንድነው?

## ትምህርት- 7

**የተራራው ስብከት፡ ሉቃ፡6፡37-49**

***መግቢያ***፡- ኢሱስ ተግባራዊ ስብከት ሰበከ፡፡ እኛ ከወትሮ በተለየ ሁኔታ እንድንኖር ያስተምረናል፡፡ ለመታዘዝ ስላለው ጥቅም ብዙ ታሪኮችን አስተማረ፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ለሕይወት አንድ ጥሩ መሠረት ለመጣል ቁልፉ ምንድነው? በዚህ መንገድ ኢየሱስን እየተከተልክ ነህ?

## ትምህርት- 8

**ዘሪ ሊዘራ ወጣ፡- ማቴ፡13፡1-13**

***መግቢያ***፡- ኢየሱስ ታሪኮችን መናገር ይወድ ነበር፡፡ በማቴ፡13 ላይ በሰው አመለካከትና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ልዩነት ተከታዮቹ እንዲረዱ ሰባት የተለያዩ ታሪኮችን ነገራቸው፡፡ የመጀመሪያው ምሳሌ ከዚህ በታች ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ቃሉ በሕይወትህ እንዳያድግ የሚያንቅ እሾህና ጭንጫ የሆነ ነገር ምንድነው? የራስህን ደቀመዛሙርት ልብ እንዴት ትገመግማለህ? ምሳሌዎችን ስለመናገር ይህ ታሪክ ምን ይነግርሃል?

## ትምህርት-9

**ኢየሱስ ይፈውሳል፡ ማር፡5፡21-43**

***መግቢያ***፡- ኢየሱስ በስብከትና በምሳሌ አስተማረ፡፡ ነገር ግን ተአምራትን በማድረግ ማስተማርም ይወድ ነበር፡፡ ኢየሱስ በአጋንንት የተያዘውን ሰው በመፈወስና የሞተውን በማስነሳት የእግዚአብሔርን ሃይልና ምህረት አሳየ፡፡ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ሃይል የሚያሳዩ ሁለት ምሳሌዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ የውይይት ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- በዚህ ታሪክ ችግር የነበራቸው እነማን ነበሩ? ከኢየሱስ እርዳታ ለማግኘት እንዴት ቀረቡ? ኢየሱስ ለዚህ ምን ምላሽ ሰጠ? ይህ ስለ ግል ችግራችን ምን ያስተምረናል?

## ትምህርት-10

**ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ላካቸው፡ ማቴ፡9፡35-10፡17**

**መግቢያ**፡- ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ከአንድ ዓመት በላይ አስተማረ። ከዚያም ሠራተኞች በእግዚአብሔር መንገሥት እንዲጨመሩ ደቀመዛሙርቱ እንዲፀልዩ ጠየቃቸው። ከዚያም ስልጣን ሰጥቶአቸው በእሥራኤል ወዳሉት ከተሞች ላካቸው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ።
ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- በዙ ድሆችን ብታይ ምን ዓይነት ምላሽ ትሰጣለህ? ኢየሱስ በዚህ ታሪክ ደቀመዛሙርትን ምን እያስተማረ ነው? ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠውን ትዕዛዝ ዛሬ ከሕይወታችን ጋር እንዴት ማዛመድ እንችላለን?

## ትምህርት- 11

**ኢየሱስ 5000 ሕዝብ መገበ፡- ማቴ፡14፡13-23**

**መግቢያ**፡- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ለመሪነት እያዘጋጀ እንዳለ ባለፈው ሳምንት ተምረን ነበር። በመጀመሪያ ብዙ ሕዝብ አስተማረ። ነገር ግን አሁን አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት በግል ማስተማር ጀመረ። በዛሬው ታሪክ ኢየሱስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መሞት ሰማ። ኢየሱስ ወደተለየ ቦታ ለብቻው መሄድ ፈለገ። ነገር ግን ሕዝቡ ተከተሉት። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- አንተ በደረሰብህ ነገር አዝነህ እያለህ ሰዎች ለሚያስፈልጋቸው ነገር ወደ አንተ መጥተው ቢያስጨንቁህ ችግሩን እንዴት ታስወግዳለህ? ሰዎች ሁል ጊዜ እኛን ፈልገው ቢመጡ ምን ዓይነት ምላሽ እንሰጣለን? በዚህ ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ደቀመሙርቱን ምን እያስተማረ ነው?

## ትምህርት-12

**ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ፡ (ክፍል-1) ዮሐ፡6፡22-42**

መግቢያ፡- ኢየሱስ 5000 ወንዶችንና ቤተሰቦቻቸውን ከመገባቸው በኂላ ሕዝቡ ተከትለውት ወደ ማዶ ተሻገሩ። በኂላም ተጨማሪ ምግብ ፈለጉ። ኢየሱስ ስለ ሕይወት እንጀራ አስተማራቸው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ምን እያስተማራቸው ነው? ሕዝቡ ኢየሱስን እንዲፈልጉ ያነሳሳቸው ምንድነው? አንተ እግዚአብሔርን ለመፈለግ የሚያነሳሳህ ምንድነው?

## ትምህርት-13

**ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ፡ (ክፍል-2)፡ ዮሐ፡6፡48-69**

**መግቢያ**፡- እንጀራን ፈልጎ ኢየሱስን ስለ ተከተለው ሕዝብ ባለፈው ሳምንት ተምረን ነበር። እነርሱ በኢየሱስ ቢያምኑ ኢየሱስ ራሱ የሕይወት እንጀራ እንደሆነ ያስተምራቸው ነበር። ይህ የሕይወት እንጀራ ዘላለማዊ ሕይወት ነው። ነገር ግን ሕዝቡ ኢየሱስ የሚለው ስላልገባቸውና ኢየሱስ ከሰማይ እንደመጣ ስላላመኑ በእርሱ ላይ አጉረመረሙ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ።
ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ሕይወት የሚሰጠው ምንድነው? ቁ.63 ስለዚህ የኢየሱስን ሥጋ የምንበላው እንዴት ነው? 12ቱ ደቀመዛሙርት ከበፊቱ ይልቅ ኢየሱስን እንዲከተሉ ያነሳሳቸው ምንድነው?

## ትምህርት-14

**የጴጥሮስ ንስሐ፡- ማቴ፡1613-27**

**መግቢያ**፡- ኢየሱስ የምድርን አገልግሎት ሲያጋምስ ደቀመዛሙርትን ፀጥ ወዳለ ሥፍራ ወሰዳቸው። ስለማንነቱ ደቀመዛሙርት ለጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ሊሰጥና ሊመጣ ስላለው ሞቱና ትንሣኤው ሊያስረዳቸው ፈለገ። ይህ በደመዛሙርቱ እድገት ላይ አዲስ ነገር የሚያዩበትና ለወደፊት አገልግሎት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ነው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ስለ ኢየሱስ እውነትን ለእኛ የሚገልጥልን ማነው? ቁ.17 በሩን የሚከፍተው ቁልፍ፣ የሰማይን በር የምንከፍትበት

ቁልፉ ምንድነው? <<ኢየሱስ የሰማይን መክፈቻ ቁልፍ ለአንተ ይሰጣሃል>> ማለት ለአንተ ምን ዓይነት ትርጉም ይሰጣሃል? ኢየሱስን መከተል የሚያስከፍለው ዋጋ ምንድነው?

## ትምህርት-15

**የኢየሱስ በሐዋሪያት ፊት መለወጥ፡- ማቴ፡17፡1-13**
**መግቢያ**፡- የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲገለጥ አንዳንዶቹ ደቀመዛሙርት እንደሚያዩት ኢየሱስ ነገራቸው። ይህን ከተናገረ ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ በተራራ ላይ ክብሩን አሳያቸው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሊያስተምራቸው የፈለገው ነገር ምንድነው? በመንፈሳዊ ሕይወትህ ልክ ተራራ ላይ እንዳለህ የተለማመድከው ልምምድ ካለ ለቡድንህ አባላት አካፍል። እንድህ ዓይነቱ ልምምድ በየዕለቱ በምትኖረው መንፈሳዊ አኗኗር ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ያመጣል?

## ትምህርት-16

**ለወንድምህ ይቅርታ ማድረግ፡- ማቴ፡18፡15-35**
**መግቢያ**፡- ኢየሱስ በቅርብ እንደሚሞት ለደመዛሙርቱ ነገራቸው። ከዚያም ከሙሴና ኤልያስ ጋር ሲነጋገር ክብሩን አሳያቸው። በደቀመዛሙርቱ ላይ በሚያምጹ ሰዎች ምን ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው አስተማራቸው። ለሚበድሏቸው ሰዎች ደግመው ደጋግመው ይቅርታ ማድረግ እንግዳ ነገር ሆኖባቸው ነበር። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ለዚህ ሰው ይቅርታ ማድረግ ከባድ ነው የምትለው ሰው አለ? ለምን? ለበደሉህ ሰዎች ይቅር ለማለት ምን ማድረግ አለብህ? ቁ.19 ላይ ያለው ሀሳብ ከዚህ ጋር ምን ተያያዥነት አለው? እንዴትስ መተርጎም አለበት?

## ትምህርት-17

**ኢየሱስን መከተል የሚያስከፍለው ዋጋ፡- ሉቃ፡9፡57-10፡1**
**መግቢያ**፡- ደቀመዛሙርቱ ከመካከላቸው ታላቅ ማን እንደሆነ ይከራከሩ ነበር። ኢየሱስ በትህትና የሚያገለግል ከሁሉም ታላቅ እንደሆነ ነገራቸው። ኢየሱስ ለመንግሥቱ ራሳቸውን ሰጥተው የሚሠሩ ተከታዮችን ፈለገ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- በዚህ ባነበብነው ክፍል ሰዎች ኢየሱስን ላለመከተል የሰጡአቸው ምክንያቶች አሉ። ኢየሱስ እነዚህን ምክንያቶች ያልተቀበለው ለምድነው? ኢየሱስ ወደ ሚልክበት ቦታ ላለመሄድና እርሱ አድርግ ያለውን ላለማድረግ የምትሰጠው ምክንያት ምንድነው? ኢየሱስ 70 ሰዎችን ወደ ከተማዋ በመላኩ ደቀመዛሙርትን ምን እያስተማረ ነው?

## <u>ትምህርት-18</u>

<u>**የጌታ ፀሎት፡- ሉቃ፡11፡1-13**</u>

<u>**መግቢያ**</u>፡- ኢየሱስ የአይሁድን በዓል ሊያከብር ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ከሃይማኖት መሪዎች ትልቅ ተቃውሞ ገጠመው። ይህ እየሆነ ባለበት ጊዜ ኢየሱስ ሲፀልይ ደቀመዛሙርት አዩ። እንዴት መፀለይ እንደሚችሉ ኢየሱስ እንዲያስተምራቸው ጠየቁት። ከዚያም የታወቀውን የጌታ ፀሎት የሚባለውን ፀሎት ሰጣቸው። ደቀመዛሙርቱ በእውነት መፀለይ ያለባቸው ፀሎት ነው። ኢየሱስ ትምህርቱን ለማጥበቅ ምሳሌ ነገራቸው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ለፀሎትህ መልስ ባይገኝ ምን ታደርጋለህ? ወደ እግዚአብሔር ስለ መቅረብ ይህ ፀሎት ምን ያስተምርሃል? እግዚአብሔር፡- አንተን፣ አስተሳሰብህን፣ስሜትህንና ፍላጎትህን የሚቀበል እንደ አንድ መልካም አባት ነው ብለህ ታስባለህ? ስለዚህ ነገር ተወያይ።

## <u>ትምህርት-19</u>

<u>**ደቀመዝሙር መሆን የሚያስከፍለው ዋጋ፡- ሉቃ፡14፡25-35**</u>

መግቢያ፡- ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ይከተሉ ነበር። ነገር ግን ደቀመዝሙር የሆኑቱ ጥቂቶች ናቸው። ሌሎች ደቀመዝሙር መሆን አልፈለጉም።
አንዳንዱ ደቀመዝሙር ላለመሆን ምክንያቶችን አቀረቡ። ስለዚህ ኢየሱስ እርሱን መከተልና የእግዚአብሔር መንግሥት አካል መሆን የሚያስከትለውን ዋጋ ነገራቸው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ኢየሱስን እንዳትከተለውና እርሱም በሕይወት ዓላማውን እንዳይፈጽም ያደረገህ በልብህ የምትወደው ነገር ወይም የምትወደው ሰው ማነው? መስቀልህን መሸከም ማለት ምን ማለት ነው? የግንቡንና የጦርነቱን ምሳሌ ከሕይወትህ ጋር እንዴት ታዛምዳለህ?

## ትምህርት-20

**የጠፋው በግና የድሪም ምሳሌ፡- ሉቃ፡15፡1-10**

***መግቢያ***፡- በመጀመሪያ ኢየሱስ ደቀመዝሙርነት የሚያስከፍለውን ዋጋ ካስተማራቸው በኂላ አሁን ደቀመዝሙር ሊሠራ ስላለው ሥራ መናገር ጀመረ፡፡ ጸፎችና ፌሪሳዊያን ኢየሱስ ከሐጢአተኞች ጋር ስለሚበላ ተቹት፡፡ ስለዚህ እነዚህን ሁለት ታሪኮችን ነገራቸው፡፡

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- የጠፉትን ለመፈለግ የእኛ ሃላፍነት ወይም ድርሻ ምንድነው? ከጌታ ቤት ርቆ ያለው ጓደኛህ ወይም የቤተሰብህ አባል ለእግዚአብሔር ምን ያህል አስፈላጊ ነው?*

## ትምህርት-21

**የጠፋው ልጅ ምሳሌ፡- ሉቃ፡15፡11-32**

***መግቢያ***፡- ስለ ጠፋው በግና ድሪም ባለው ሳምንት ተምረን ነበር፡፡ በዚህ ሳምንት ኢየሱስ ሌላ ምሳሌ ነገረ፡፡ ይህ ምሳሌ ስለ ጠፋው ልጅ ነው፡፡ ይህንን ምሳሌ ስትሰማ አንተ የትኛውን ሰው እንደምትመስል አስብ፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- በታሪኩ ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች የትኛውን ትመስላለህ? ለምን?*

## ትምህርት-22

**የአልዓዛር ከሞት መነሣት፡ ዮሐ፡11፡1-49**

*መግቢያ፡- ኢየሱስ በቅርቡ በኢየረሳሌም ሞት እንደሚገጥመው ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸው፡፡ ነገር ግን ኢየሱስን መከተላቸውን ቀጠሉ፡፡ በዛሬው ታሪክ ኢየሱስ ስለራሱ ማንነት፣ስለ ሞትና ስለ ሕይወት አስረግጦ ተናገረ፡፡ ይህንን ታላቅ ተአምር ከእግዚአብሔር ቃል ስማ፡፡*

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ቶማስ እንዳደረገው ኢየሱስን ስትከተል ችግር ቢገጥምህ ምን ምላሽ ትሰጣለህ? ለማርታና ማሪያም በፈለጉበት ጊዜ ፍላጎታቸው ሳይሟላ እንደዘገየባቸው የፈለከው ነገር ሳይሟላ ቢዘገይ ምን ምላሽ ትሰጣለህ? አንድ የምትወደው ሰው ቢሞት ምን ታደርጋለህ? ተስፋ እንደሌለው ሰው የሀዘን ማቅ ትለብሳለህ? 1ተሰ፡4፡13-18 አንብብ፡፡*

## ትምህርት-23

**ሌሎችን ማገልገል፡- ማር፡10፡32-45**

*መግቢያ፡- ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሣው ካህናት በጣም ተቆጡ፡፡ ደቀመዛሙርት በየቀኑ በፍርሃት እየተዋጡ ሄዱ፡፡ እነርሱ ወደፊት ለምትመጣው ቤተክርስቲያን ቆራጥ መሪዎች እንዲሆኑ ኢየሱስ ማስተማሩን ቀጠለ፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- በእግዚአብሔር ቤት እያለን ስልጣንን ለመያዝ ያደረግንበትን የውድድር ጊዜ ተወያዩ፡፡ በንጹሕ ልቦና ለስልጣን መወዳደርና፣ ራስን በመውደድ መንፈስ ለስልጣን መወዳደር የትኛው ስህተት ነው? በቡድንህ የአገልጋይነትን አመለካከት እንዴት ታሳያለህ? በዚህ ሳምንት አባላትን ለማገልገል ምን ማድረግ አለብህ?*

## ትምህርት-24

**ኢየሱስ በድል ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፡ ሉቃ፡19፡28-48**

***መግቢያ***፡- *የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን ስለሚጠሉት በቅርብ ሊገድሉት ዕቅድ አወጡ፡፡ በዛሬው ታሪክ ኢየሱስ ንጉሥ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ፡፡ ይህ የድልና የደስታ ቀን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ በቅርቡ እንደሚሞት ያውቅ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሣ የኢየሱስ ደስታ አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ ይል ነበር፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-*

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- እስቲ ራስህን በደመዛሙርት ቦታ አስቀምጥ፤ኢየሱስ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያልፍ ብታይ ምን ታስብ ነበር? ለምን? ኢየሱስ ለምን አለቀሰ? ኢየሱስን ለመግደል ስለሚፈልጉ ሰዎች ምን ይሰማህ ነበር? እያንዳንዱ መሪ በስሜቱ ላይ ስለሚያጋጥመው ጫና ምን ይሰማህ ነበር?*

## ትምህርት-25

**ኢየሱስ የደቀመዛሙርትን እግር አጠበ፡ ዮሐ፡13፡1-26**

***መግቢያ***፡- *ኢየሱስ ንጉሥ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ገብቶ ቤተመቅደስን አጠራ፡፡ ሕዝቡ ኢየሱስን ስለ ግብር መክፈል፣ስለ ጋብቻና ስለ ራሱ ሥልጣን ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቁ፡፡ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ስለ መጨረሻው ጊዜ ምልክቶች ነገራቸው። ይህ በእንዲህ እንዳለ አስቆሮቱ ይሁዳ ኢየሱስን ለሊቀ ካህናት አሳልፎ ሊሰጥ ተማከረ፡፡ ይህ ሁሉ እየሆነ ባለበት ጊዜ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የፋሲካውን እራት ሊበላ ፈለገ፡፡ እንዲሁም በእርሱ ላይ ሊሆን ስላለው ነገር ሊያስተምራቸው ፈለገ፡፡ ኢየሱስም በመንግሥቱ የታላቅ መሪ አርአያ (ሞዴል) መሆኑን አሳያቸው፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ኢየሱስ ያገለገለው በድካም ነው ወይስ በትጋት? አንተስ እንዴት ታገለግላለህ? እግርን ማጠብ አገልግሎት ነው። እንዲህ ዓይነት አገልግሎት በየዕለት ሕይወትህ? በቡድንህ? በቤተሰብህ? በቤተክርስቲያንህ? ምን ይመስላል?

## ትምህርት-26

**ኢየሱስ ወደ አብ የሚያደርስ መንገድ፡ ዮሐ፡14፡1-18**

**መግቢያ**፡- ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በነበረው የመጨረሻው እራት ጊዜ ወርዶ እግራቸውን አጠበ። ከዚያም ከእነርሱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠውና ጴጥሮስ ደግሞ እንደሚክደው ነገራቸው። ሁሉም በነገሩ እጅግ ተገረሙ፤ ጴጥሮስም ‹‹እኔ አልክድህም›› አለው። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ማንነቱና ከትንሣኤው በኋላ ወዴት እንደሚሄድ በግልጽ ነገራቸው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ብዙ መንገድ አለ ለሚሉ ሰዎች ምን ዓይነት ምላሽ ትሰጣለህ? ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ከሰራው ሥራ የበለጠ ይሰራሉ ማለት ምን ማለት ነው? ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንማራለን?

## ትምህርት-27

**ኢየሱስ እውነተኛ የወይን ግንድ፡ ዮሐ፡15፡1-17**

**መግቢያ**፡- ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ መንገድ፣እውነትና ሕይወት እርሱ እንደሆነ ካስተማራቸው በኋላ እነርሱም ሕይወታቸውን በእርሱ ላይ እንዲያኖሩ ረዳቸው። ሕይወታቸውን ከወይኑ ግንድ፣ከቅርንጫፎቹና ከፍሬው ትርጉም ጋር በማነጻጸር በእርሱ መኖር የሚችሉበትን ምስጢር ለደቀመዛሙርቱ አስተማራቸው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- እኛ እንዴት ከኢየሱስ ጋር ተጣብቀን መኖር እንችላለን? የመንፈስን ፍሬ በማፍራት ረገድ ሕይወትህ ምን ይመስላል? ለምን? አንዳንድ ደቀመዛሙርት ለኢየሱስ እንደ ጓደኛ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ እንደ ወንድምና እንደ እህት ሲቀርቡት ደቀመዛሙርቱ ከዚህ ምን ይማራሉ?

## ***ትምህርት-28***

**<u>ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ፀለየ፡ ማር፡14፡ 32-42</u>**

***<u>መግቢያ</u>***፡- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ስለ እውነተኛ የወይን ግንድ ካስተማራቸው በኂላ ጴጥሮስን ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥረው እንደፈለገና ከዚህ የተነሣ ጴጥሮስ እንደሚክደው አስጠነቀቀው፡፡ ከዚያም ወደ ኦልብ ተራራ ሊፀልዩ ሄዱ፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ስለ ፀሎት ምን እንማራለን? ኢየሱስ የፀለየውን ፀሎት እንደገና አንብብ፡፡ እርሱ እንዴት እንደፀለየ ተወያይ፡፡*

## ***ትምህርት-29***

**<u>የጴጥሮስ ክህደት፡ ሉቃ፡22፡54-62</u>**

***<u>መግቢያ</u>***፡- ጴጥሮስ ኢየሱስን እንደሚክደው ባለፈው ሳምንት ተምረን ነበር፡፡ ከዚያም ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ፀለየ፡፡ ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ እንቅልፍ ወስዶአቸው ነበር፡፡ ከዚያም የቤተመቅደስ አዛዦች ኢየሱስን ሊይዙት መጡ፡፡ ደቀመዛሙርቱ ፈርተው ሸሹ፡፡ ቀጥሎ የሆነው ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቧል፡

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ዛሬ ኢየሱስን የምንክድባቸው መንገዶች ምንድናቸው? በሕይወታችን ላይ የሚነሱትን የሐጢአት ፈተናዎች እንዴት ማሸነፍ እንችላለን? ከደቀመዛሙርቱ ምሳሌ ምን ትማራለህ? ከኢየሱስ ምሳሌ ምን ትማራለህ? እንደ ጴጥሮስ አንድን ነገር ስታደርግ ክርስቶስ እንዳየህ የተሰማህ ጊዜ መቼ ነው? ያደረከው ነገር ምንድነው?*

## ***ትምህርት-30***

**<u>የኢየሱስ ስቅለት፡ ማር፡15፡24-39</u>**

***<u>መግቢያ</u>***፡- የስቅለት ታሪክ በአራቱ ወንጌላት ማለትም በማቴዎስ፣በማርቆስ፣በሉቃስና በዮሐንስ ወንጌል ይገኛል፡፡ የታሪኩን ጠቅላላ ክፍል በሚቀጥለው ሳምንት ትምህርት በማንበብ የበለጠውን መማር ትችላለህ፡፡ ካህናትና ጵላጦስ ኢየሱስን በመግረፍ አሰቃዩት፡፡ ወታደሮቹ ጎልጎታ ወደሚባል ቦታ አምጥተው እዚያው ሰቀሉት፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- አንተ በዚህ ታሪክ ውስጥ ብትሆን በታሪኩ ውስጥ ከተገለጹት ሰዎች የትኛውን ትመስል ነበር? ለምን? በስቅለቱ ታሪክ ልብህን የሚነካው የትኛው ክፍል ነው? ለምን? ከክርስቶስ ጋር መሰቀል ለአንተ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?* (ገላ፡2፡20)

## <u>ትምህርት-31</u>

**<u>ኢየሱስ ሕያው ሆነ! ሉቃ:24:1-49</u>**

***<u>ለመሪው፡- ይህ ታሪክ ረጅም ስለሆነ ሁለት ሰዎች ተከፋፍለው እንዲናገሩ ልታደርግ ትችላለህ።</u>***

***<u>መግቢያ</u>***፡- ኢየሱስ ሞትን ሞቶ ዕዳችንን ከፈለው። ሰንበት እየቀረበ ስለነበረ ሁለት ሰዎች ኢየሱስን ቶሎ ወስደው በአዲስ መቃብር ቀበሩት። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ሲከተሉት የነበሩ ሴቶች ኢየሱስን የቀበሩበትን መቃብር አይተው በሁለተኛው ቀን ሽቱ ይዘው ወደ መቃብሩ ለመምጣት አቀዱ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

*ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ኢየሱስ ሲሞት ካየኸው በኋላ ከሞት ተነሥቶ ለአንተ ቢታይ ምን ዓይነት ምላሽ ትሰጥ ነበር? ኢየሱስ ስለ ሞቱና ስለ ትንሣኤው ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ታውቃለህ? ኢየሱስ ስለ ትንሣኤው ለደቀመዛሙርቱ እንዴት አረጋገጠ?*

## <u>ትምህርት-32</u>

**<u>ኢየሱስ ለጴጥሮስ ትዕዛዝ ሰጠው፡ ዮሐ:21:1-23</u>**

***<u>መግቢያ</u>***፡- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ወደ ገሊላ እንዲያልፉና እዚያው እንደሚያገኛቸው ነገራቸው። ጴጥሮስ ኢየሱስን ስለካደው በጣም አዝኖ ነበር። አሣ ለማጥመድ ወሰነ። ኢየሱስ ው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

*ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ መረባቸውን ወደ ቀኝ እንዲጥሉ ካዘዛቸው በኋላና ብዙ ዓሣዎችን ከያዙ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ያሰቡት ምንድነው? ኢየሱስን መውደዳችንን እንዴት ማሳየት እንችላለን? አንድ ደቀመዝሙር ወደ ኋላ ቢያፈገፍግ ምን ታደርጋለህ?*

## <u>ትምህርት-33</u>

**<u>የምንፈስ ቅዱስ ተስፋ፡ ሐዋ:1:1-10</u>**

***<u>መግቢያ</u>***፡- ኢየሱስ ለብዙ ቀናት ለደቀመዛሙርት ታየ። መጽሐፍትን እንዲያውቁ አእምሮአቸውን ከፈተ። ከዚያም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እስኪቀበሉ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዘዛቸው። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ተስፋ ነው። ምን ያህል ጊዜ መጠበቅ እንደነበረባቸው ኢየሱስ ግልጽ አላደረገላቸውም። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

*ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ*

ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ‹‹በኢየሩሳሌም፣በይሁዳ፣በሰማሪያና እስከ ምድር ዳርቻ ምክሮቼ ትሆናላችሁ›› ያለውን ቃል አንተ እንዴት ልትተገብረው ትችላለህ?

## ትምህርት-34

**የበዓለ ሃምሳ (ጴንጤ ቆስጤ) ቀን፡ ሐዋ፡2፡1-16**

***መግቢያ***፡- ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ካዮ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ወደ ላይኛው ክፍል ገቡ። በዚያው እየፀለዩ ይጠብቁ ነበር። መጽሐፍትን ይመረምሩ ነበር። ከእግዚአብሔር የተሰጠው ተስፋ ቃል ሲፈጸም ካዩ በኋላ የሚያደርጉትን አጡ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ሰዎቹ አመንትተው ‹‹እንጃ ይህ ምን ይሆን?›› አሉ። እጅግ ተደነቁ። መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ሲሰራ ሰዎች ቢያዩ ምን ምላሽ ትሰጣለህ? መንፈስ ቅዱስ ባንተ ውስጥ መሥራቱን በምን ታውቃለህ?

## ትምህርት-35

**ጴጥሮስ፡ ሐዋ፡3፡1-31**

***መግቢያ***፡- መንፈስ ቅዱስ በደቀመዛሙርት ሕይወት ስር ነቀል ለውጥ አምጥቷል። ኢየሱስ እንዳስተማራቸው መኖር ጀመሩ። በቤታቸውና በቤተመቅደሱ ያመልኩ ነበር። ተአምራትን ማድረግ ጀመሩ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ጴጥሮስ የተለወጠው እንዴት ነበር? ጴጥሮስ ለሕዝቡ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምን ነበር? ከጴጥሮስ ስብከት ክብሩን የሚቀበለው ማነው?

## ትምህርት-36

**የዲያቆናት (አገልጋዮች) መሾም፡ ሐዋ፡6፡1-8**

***መግቢያ***፡- ደቀመዛሙርቱ በቁጥር እየጨመሩ ሄዱ። አብዛኛዎቹ ከእሥራኤል ውጪ ይኖሩ የነበሩ ግሪክ አይሁድ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች አሁን በኢየሩሳሌም ከዕብራዊያን አይሁድ ጋር መኖር ጀመሩ። ዛሬም በቤተክርስቲያን ችግር እንዳለ ሁሉ በእነርሱም መካከል ችግር ነበር። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን አንብብ። በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ። ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- በደቀመዛሙርት መካከል የሚፈጠረውን ችግር ስለማስወገድ ከዚህ የምንማረው ምንድነው?

## ትምህርት-37

**ስደት፡ ሐዋ፡7፡54-8፡4**

***መግቢያ***፡- ደቀመዛሙርቱ ስለ እግዚአብሔር ቢሰደዱም እግዚአብሔር አብዝቶ ባረካቸው፡፡ ከቤተክርስቲያን ዲያቆናት አንዱ እስጢፋኖስ ነበር፡፡ እስጢፋኖስ የእግዚአብሔር ፀጋና ሃይል የነበረው ሰው ነበር፡፡ እርሱ በሕዝቡ መካከል ታላላቅ ተአምራትን ያደርግ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ የአይሁድ አለቆች ይቃወሙትና ሌሎችን በእርሱ ላይ ያስነሱ ነበር፡፡ እርሱን ይዘው ወደ አይሁድ አለቆች ሲያመጡት እዛም ስለ ኢየሱስ ይመሰክር ነበር፡፡ ታሪኩ ከእዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- ስደት ቢገጥምህ እንዴት ትወጠዋለህ? ከስደት የተነሳ የሆነው መልካም ነገር ምንድነው? ለሌሎች ለመመስከር ራስህን እንዴት ታዘጋጃለህ?

## ትምህርት-38

**ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ደቀመዝሙር አደረገው፡ ሐዋ፡16፡1-5 እና 2ጢሞ፡2፡1-5**

***መግቢያ***፡- ኢየሱስ ለራሳቸው ደቀመዝሙር ከሆኑ በኂላ ሌሎችን ደቀመዝሙር የሚያደርጉ ሰዎችን ሰብስቦ እንዳስተማረ ደቀመዛሙርቱም በተራቸው የኢየሱስን ሞዴል ተከተሉ፡፡ ባርናባስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ካሉ ደቀመዛሙርት አንዱ ነበር፡፡ ባርናባስ ጳውሎስን ስለ ደቀመዝሙርነት አስተማረው፡፡ ከዚያም ጳውሎስ ጢሞቴዎስን መረጠ፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡ በአራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርግ፡፡ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡- 2ጢሞ፡2፡1-2 አንብብ፡፡ ሌሎችን ደቀመዝሙር ስለ ማድረግ ምን እንማራለን? አንተ ደቀመዝሙር የምታደርገውን ሰው ማነው? በዚህ ኢየሱስን መከተል ትምህርት ጉዞ ውስጥ ሌሎች ከራስህ ጋር እንዲጓዙ አድርግ፡፡